40

# በትራንስፖርት ባለስልጣን
# የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ
## አሰራር መመሪያ 683/2013

መጋቢት/2007
አዲስ አበባ

# የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

# አሠራር መመሪያ 01/2007

## መግቢያ

የትራንስፖርት ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 600/2000 በአንቀጽ 5 /አምስት/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሠጣጥ አስመልክቶ በህዳር 2003 ዓ.ም የመጀመሪያውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አሰራር መመሪያ አውጥቶ ለሁሉም ክልል አሰራጭቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከ2004 እስከ 2006 ዓ.ም የተተገበረውን መመሪያ በትግበራው ወቅት የታዩ ክፍተቶችን መሰረት በማድረግ የተሻሻለውንና የቀድሞውን ሊተካ የሚችል በማድረግ የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. ዓላማ

"ግልፅ ቀልጣፋ ጥራት ያለው የምዝገባ፣ የስልጠና፣ የፈተና፣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳት አገልግሎት አሰጣጥ ለማስፈን የሚያስችል አሰራር ለማስፈን ነው፡፡"

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰራር መመሪያ "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በስተቀር በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 2 እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ 600/2000 አንቀጽ 2 /ሁለት/ የተዘረዘሩት ቃላት ትርጉም በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

የሚከተሉት ተጨማሪ ቃላትም ከዚህ በታች የተዘረዘረው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

1. “ባለሥልጣን” ማለት ትራንስፖርት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ማለት ነው፡፡
2. “ተሃድሶ” ማለት አንድ አሽከርካሪ የማሽከርከር ብቃቱ አነስተኛ መሆን ብቻ ሳይሆን በትራፊክ ክስ (ሪኮርድ) ሲመዘገብበት በካሪኩለሙ መሠረት የሚሰጥ ስልጠና ነው፡፡
3. “ልዩ ስልጠና” ማለት አንድ አሽከርካሪ ከነበረበት ምድብ ወደ ሌላ ምድብ እንዲሁም ከነበረበት ምድብ ከታች ወደ ላይ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን ለመለወጥ ሲፈልግ ምድቡ ወይም ንዑስ ምድቡ የሚጠይቀው ተጨማሪ ስልጠና ነው ፡፡
4. “የሰልጣኝ መታወቂያ” ማለት ፈቃድ ሰጪው በሚያወጣው መስፈርት መሠረት የማሰልጠኛ ተቋሙ ለሰልጣኙ አዘጋጅቶ የሚሰጠው መታወቂያ ነው ፡፡
5. “የአሰልጣኝ መታወቂያ” ማለት ፈቃድ ሰጪው በሚያወጣው መስፈርት መሠረት የማሰልጠኛ ተቋሙ ለአሰልጣኙ አዘጋጅቶ የሚሰጠው መታወቂያ ነው፡፡
6. “ተቆጣጣሪ” ማለት ከምዝገባ እስከ ብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት አሰጣጥና አጠቃቀም ያለውን ሂደት የሚቆጣጠር የፈቃድ ሰጪው አካል ሠራተኛ ነው፡፡
7. “ፈቃድ ሰጪ” ማለት ብቃት የተረጋገጠበት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጥ በባለስልጣኑ የዕውቅና ሠርተፍኬት የተሰጠው ማንኛውም የመንግስት አካል ነው ፡፡
8. “ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ” ማለት ስምንተኛ ክፍል ጨርሶ ለፈተና መቅረቡን የሚያሳይ የት/ት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡፡
9. “አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀ” ማለት የአራተኛ ክፍል መደበኛ ትምህርት ያጠናቀቀበትን የት/ት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡፡



## ክፍል ሁለት

## ስለ አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ

4. **ለአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስልጠና ስለሚጠይቁ ቅድመ ሁኔታዎች**

1. የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ፈቃድ ከተሰጠውና በአካባቢዉ ከሚገኝ ከታወቀ የመንግሥት ወይም የግል የህክምና ተቋም ::
2. የቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የልደት ሠርተፍኬት ወረቀት
3. ከሞተር ባይስክልና ከአዉቶሞቢል ስልጣኝ በስተቀር በሌሎች ምድቦች ላይ የሚያመለክት ስልጣኝ የዕድሜዉ ሁኔታ አጠራጣሪ ሆኖ ከተገኘ የልደት ሠርተፍኬት ማስረጃ እንዲያቀርብ ይገደዳል::
4. ለምድቡ የተቀመጠውን አግባብነት ያለውን የትምህርት ማስረጃ::
5. አንድ ሰልጣኝ በአከባቢው 9በከተማው፤ዞን፤ክልል) ያለውን ማሰልጠኛ ተቋም አልፎ ወደሌላ አከባቢ (ከተማ፤ዞን፤ክልል) በመሄድ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ አይችልም::
6. ክልሎች መቆጣጠር አቅም እስካላቸው ድረስ አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ስልጠና የንድፈ ሀሳብ ስልጠና በማታ ክፍለ ጊዜ መስጠት ይቻላል :: ነገር ግን የተግባር ስልጠና በቀን ክፍለ ጊዜ ብቻ መሰጠት አለበት ::
7. አካል ጉዳተኞች አውቶሞቢል መንዳት ይችላሉ ተብሎ ከሆስፒታል ማስረጃ ካመጡ መሰልጠን እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ መውሰድ ይችላሉ::
8. ማሰልጠኛ ተቋሙ ለአካል ጉዳተኛው የሚሆን ተመጣጣኝ ቴክኖሎጂ ያለው ተሽከርካሪ ከሌለው ሰልጣኙ በሚያቀርበው ተመጣጣኝ ቴክኖሎጂ ያለው ተሽከርካሪ አሰልጥኖ ማስፈተን ይችላል::

5. **ስለሰልጣኞች ምዝገባ**

1. ሰልጣኞች በፖስታ ወይም በኢ-ሜል፣ ወይም በግንባር በመቅረብ በማሠልጠኛ ተቋማት መመዝገብ ይችላሉ ::
2. ማንኛውም ሰልጣኝ ሥልጠና ከመጀመሩ በፊት 3/ሶስት/ ቀን አስቀድሞ በማሠልጠኛ ተቋማት መመዝገብ አለበት ::

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

4. ሰልጣኙ የተቋሙን የምዝገባ ቁጥር የያዘ የስልጠና መታወቂያ (Learners permit) መያዝ አለበት ::
5. ማሠልጠኛ ተቋሙ የተመዘገቡትን ሰልጣኞች ስም ዝርዝር በቀጥታ መስመር (On line) ወይም ምዝገባውን ባጠናቀቀበት ቀጣይ ቀን ከሰልጣኞች መረጃ ጋር አባሪ አድርጎ ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪ አካል ማስተላለፍ አለበት::
6. የሠልጣኞች መረጃ ፎቶ ኮፒዉ ከዋናው (ከኦርጅናል) ጋር ተገናዝቦና ተረጋግጦ ፎቶ ኮፒው በፈቃድ ሰጪው አካል ሊያዝ ይገባል::

## 6. የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና በተመለከተ

1. የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠናው ባለሥልጣኑ ባወጣው ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት በአንድ ተቋም መሰጠት አለበት ::
2. የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና በካሪኩለሙ መሠረት ተዋህዶ ከተሰጠ በኋላ የሙከራ ፈተና በኮምፒዩተር በማሠልጠኛ ተቋሙ ልምምድ መሰጠት አለበት::
3. ለአውቶሞቢል ምድብ ሰልጣኞች 20 ሰዓት ከ8-12 መቀመጫ ባላቸው ተሽከርካሪዎች የተግባር ስልጠና ይሰጣል::
4. የማሠልጠኛ ተቋሙ ለፈተና ብቁ የሆኑትን ሰልጣኞች ስም ዝርዝር በኮምፒዩተር መረብ ወይም በhard copy ለፈቃድ ሰጪው አካል ማስተላለፍ አለበት ::
5. የንድፈ ሀሳብ ስልጠና በቀን 4 /አራት/ ሰዓት መሰጠት አለበት::
6. አንድ ተሽከርካሪ በቀን ከአስር ሰዓት በላይ ማሰልጠን የለበትም::
7. አንድ ሰልጣኝ በቀን አንድ ሰዓት የተግባር ስልጠና መሰልጠን አለበት::
8. የማሰልጠኛተሽከርካሪ የዓመታዊ ቴክኒክ ምርመራ ያደረገ መሆን አለበት::

## 7. ስለንድፈ ሀሳብ ፈተና

1. ማንኛውም ተፈታኝ ወደ ፈተና ጣቢያ ሲመጣ የስልጠና መከታተያ መታወቂያ ካርድ ይዞ ካልቀረበ ወደ ፈተና አዳራሽ መግባት አይችልም::
2. ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ፈታኞች ስለፈተናው አሰራር በግልፅ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት አለባቸው::
3. ፈተናው በሴኩሪቲ ካሜራ ቁጥጥር እየተደረገበት ለእያንዳንዱ ተፈታኝ በተዘጋጀ ኮምፒዩተር ላይ ይሰጣል::

17. የጽሑፍ ፈተና የወደቀ ተፈታኝ ያለምንም ሥልጠና በተጨማሪ ሁለት የፈተና ዕድል ተሰጥቶት እንዲፈተን ይደረጋል:: ሶስት ጊዜ ተፈትኖ የወደቀ ሠልጣኝ እንደገና በየ1 ወሩ መፈተን ይችላል ::

18. የጽሑፍ ፈተና አልፎ የተግባር ፈተና ለወደቀ ተፈታኝ የአንድ ጊዜ የጽሑፍ ፈተና ውጤት ለአንድ ዓመት ብቻ ያገለግላል:: ከአንድ ዓመት በኋላ ለሚመጣ ተፈታኝ የጽሑፍ ፈተና እንደገና እንዲወስድ ይደረጋል::

19. በጽሑፍ ፈተና አሠጣጥ ላይ ቅሬታ ያለው ተፈታኝ ቅሬታውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጪ ኃላፊ ማቅረብ ይኖርበታል :: በኃላፊው ምላሽ ካልረካ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል:: የበላይ ኃላፊ ጊዜያዊ አጣሪ ኮሚቴ አቋቁሞ ያስመረምራል:: ሥልጠናውን የሰጠው ተቋም የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው አባል ሆኖ እንዲሠራ ይደረጋል:: ውሳኔ ይሰጣል::

20. በፈተና ወቅት ማሰልጠኛ ተቋማት ተፈታኞችን ለፈተና ከማቅረብ በስተቀር ፈተና በሚሰጥበት አካባቢ መገኘት የተከለከለ ነው::

## 8. ስለተግባር ፈተና አሰጣጥ

1. ፈታኙ የሰልጣኝ መታወቂያ (Learner Permit) በማየት ማንነቱን ያረጋግጣል::
2. ፈታኙ የተፈታኙን መታወቂያ በማረጋገጥና በማስገባት በፈተና ማረጋገጫ ዝርዝር ቼክ ሊስት መሠረት ፈተናውን በሚገባ ያከናውናል::
3. በተፈታኙ ቼክ ሊስት ላይ ያሉትን ነጥቦች በሚገባ በመሙላትና ተፈታኙ የሰራውን ስህተት በየርዕሱ አቅጣጫ መጻፍ አለበት::
4. ፈተናው በ40 ደቂቃ ያህል በተዘጋጀው ቼክ ሊስት መሠረት የከተማ፣ የዳገትና የቁልቁለት፣ የሜዳ፣ የጠመዝማዛ፣ የምልክት መብራት፣ መስመር ... ወዘተ በተሟሉበት የተመረጡ መስመሮች /ሩትስ/ ላይ ተፈታኝ ብቻውን ራሱን ችሎ (Solo Driving) በማሽከርከር ይከናወናል::
5. የተግባር ፈተናው በሴኩሪቲ ካሜራና በሚፈትኑ ፈታኝ ቴክኒሽያኖች በሚሞሉት ቼክ ሊስት አማካኝነት መከናወን አለበት::
6. ፈታኙ ፈተናውን እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ የቼክ ሊስቱን ውጤት በኮምፒዩተር መረብ ማስተላለፍ አለበት::
7. የተግባር ፈተና ዝቅተኛው የማለፊያ ነጥብ 74% ነው::
8. ፈተናው በሴኩሪቲ ካሜራ የታገዘ ሲሰጥ ተፈታኙ ብቻውን በሚፈተንበት ወቅት ስላከናወናቸው ተግባራት ተቀርጾ በፕሮግራም የብዙ ተፈታኞች ፈተና በአንድ ላይ መገምገም አለበት::
9. ፈታኝ ሠራተኛው የሚቆምበት የፈተና መስመር ቁጥርና የራሱን መለያ ኮድ ቁጥር ደረቱ ላይ ማንጠልጠል አለበት::
10. የተግባር ፈተና ከወደቀ የወደቀበትን የፈተና ዓይነት እንዲስለጥን ሳይገደድ በቅድሚያ ለ3 ጊዜ በተከታታይ መፈተን ይችላል:: 3 /ሶስት/ ጊዜ ተፈትኖ ከወደቀ የተፈታኙ



Federal Democratic Republic of Ethiopia Transport Authority No. 1

የመፈተን ጥያቄ እስካለ ድረስ በየ 1 ወር ልዩነት አንድ ጊዜ ፈተናውን እስኪያልፍ ድረስ መፈተን ይችላል፡፡

11. በአውቶሞቢል ምድብ ሰልጣኞች የተግባር ፈተና ከ8-12 መቀመጫ ባላቸው ተሽከርካሪዎች ብቻ መሆን አለበት፡፡

12. የመሰናክል ፈተና ከከተማ አንዳድ ተግባር ፈተና ጋር ለሁሉም ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድቦች ይሰጣል፡፡

13. አንድ ተፈታኝ በመሰናክል የተግባር ፈተና ወቅት አንድ ጉቶ ከጣለ በዚያ ምድብ የተሰጠዉን ነጥብ ሙሉ ለሙሉ ያጣል፡፡ (ለምሳሌ፣በአንድ ቁጥር የመሰናክል አሰራር ወቅት አንድ ጉቶ ከጣለ ለአንድ ቁጥር የመሰናክል አሰራር የተሰጠዉን ነጥብ ሙሉ ለሙሉ አያገኝም ማለት ነዉ)

14. የሞተር ሳይክል የመሰናክል የተግባር ፈተና ተፈታኝ አንድ ጉቶ ከጣለ የመሰናክል ውጤቱን ወደሚሄድበት አቅጣጫ የተሰጠውን ነጥብ ሙሉ በሙሉ ያጣል፡፡

15. የጽሁፍ ፈተና የወደቀ ሰልጣኝ የተግባር ፈተና መፈተን ይችላል ፤ እንደዚሁም የተግባር ፈተና የወደቀ የጽሁፍ ፈተና መፈተን ይችላል፡፡

16. አንድ ተፈታኝ በፈተና ውጤት ቅሬታ ከተሰማው ለአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የሥራ ኃላፊውን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ቅሬታ አቅራቢው በኃላፊው ምላሽ ካልረካ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡ ኃላፊውም የማሠልጠኛ ተቋሙ አባልነት ያለበት ኮሚቴ አቋቁሞ እንዲጣራ ያደርጋል፡፡ ሆኖም አንድ ወር ባለፈው ጉዳዩ ቅሬታ ማቅረብ አይቻልም፡፡

17. የትራፊክ ኮምፕሌክስ የመፈተኛ ሜዳ በሌለበት የሚፈተኑ ተፈታኞች ብቻቸውን እያሽከረከሩ በቪዲዮ ካሜራ እየተቀረፁ ወይም ታዛቢዎች ፈታኞች በሌላ ተሽከርካሪ ከኋላ በመከተል የፈተናውን ሁኔታ መከታተልና መፈተን አለባቸው፡፡

18. የታዛቢዎች ቁጥር ሶስትና ከዚያ በላይ ሆኖ ከተለያዩ አግባብነት ካላቸው ክፍሎች የተውጣጡ ጥሩ ስነ-ምግባር ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

19. አንድ አሽከርካሪ የተግባር ፈተና በሚፈተንበት ጊዜ ከፈተና ካርታ ውጪ እስካልወጣ ድረስ በሰራው ስህተት ነጥብ እንዲቀነስበት ይደረጋል እንጂ ፈተናውን እንዲያቋርጥ ማድረግ አይቻልም ፡፡

20. በሞተር ሳይክል በመሰናክል ውስጥ በሚያሽከረክርበት ጊዜ እግሩ መሬት ከነካ የሚፈተንበት አቅጣጫ የተሰጠውን ነጥብ ብቻ ሙሉ በሙሉ ያጣል፡፡

21. የተግባር ፈተና አልፎ የጽሑፍ ፈተና ለወደቀ ተፈታኝ የአንድ ጊዜ የተግባር ፈተና ውጤት ለአንድ ዓመት ብቻ ያገለግላል፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላ ለሚመጣ ተፈታኝ የተግባር ፈተና እንደገና እንዲወስድ ይደረጋል፡፡

## 8.1 የሞተር ሳይክል የተግባር አነዳድ ፈተና ቼክ ሊስት

| ተ.ቁ | ይዘቶች | የተሰጠ ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | አንድ አሽከርካሪ ተሽከረካሪውን ከማንቀሳቀሱ በፊት መፈተሽ የሚገባውን በተግባር ማሳየት | 3 |
| 2 | ሞተር ሳይክል ላይ አወጣጥና አቀማመጥ፤ | 3 |
| 3 | የሞተር ሳይክል ሞተር ቁልፍ አገባብና ሞተር አነሳስ፤ | 3 |
| 4 | በመስታወት ግራና ቀኝ ተመልክቶ ሚዛን ጠብቆ መነሳትን | 3 |
| 5 | ማርሽ አጨማመርና አቀናነስ ችሎታ | 3 |
| 6 | ወደ ግራ የመታጠፍ ችሎታ | 3 |
| 7 | ወደ ቀኝ የመታጠፍ ችሎታ | 3 |
| 8 | የመቅደም ችሎታ | 3 |
| 9 | የማስቀደም ችሎታ | 3 |
| 10 | ርቀትን ጠብቆ የማሽከርከር ችሎታ | 3 |
| 11 | ፍጥነቱን ተቆጣጥሮ የማሽከርከር ችሎታ | 3 |
| 12 | የመንገድ መስመር ምልክቶችን የማወቅና የመረዳት ችሎታ | 2 |
| 13 | መብራት የሚያስተላለፉት ምልዕክት የመፈፀም ችሎታ | 2 |
| 14 | የድንገተኛ አቋቋም ችሎታ | 3 |
| 15 | የዝግ አነዳድ ችሎታው | 3 |
| 16 | የመሪና የባላንስ አጠባበቅ ችሎታ | 4 |
| 17 | ረድፍ አጠባበቅና አለዋወጡ | 4 |
| 18 | ኩርባ አዟዟር ችሎታ | 4 |
| 19 | የእግር ፍሬን አጠቃቀም ችሎታው ከተለያየ የመንገድና የትራፊክ ሁኔታ ጋር | 3 |
| 20 | አካባቢን የመቃኘት ችሎታውና ሌሎች እንዲያዩት የሚያደርገው ጥረት | 3 |
| 21 | በመንገድ ላይ የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች ለማለፍ የሚያደርገው ጥንቃቄ | 3 |
| 22 | መስቀለኛ መንገድ ላይ የሚያደርገው ጥንቃቄ | 3 |
| 23 | አቋቋም ችሎታው | 3 |
| 24 | የመሰናክል ፈተና (Zig Zag) ወደ ፊት መሄድ | 15 |
| 25 | የመሰናክል ፈተና ወደ ኋላ መመለስ | 15 |
| | ድምር | 100% |

## 8.2 የአውቶሞቢል፣ የታክሲ 2 ፣ የደረቅ 1 እና የህዝብ 1 ምድብ የተግባር ፈተና ቼክ ሊስት

| ተ.ቁ | የፈተና ይዘት | የተሰጠ ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | **ቅድመ ጉዞ በሚመለከት** | |
| 1.1 | አንድ አሽከርካሪ ተሽከረካሪውን ከማንቀሳቀሱ በፊት መፈተሽ የሚገባውን በተግባር ማሳየት | 2 |
| 1.2 | በር አከፋፈትና አዘጋግ /ጋቢና አገባብ/ | 1 |
| 1.3 | መቀመጫ ወንበር፣ መስታወት፣ የደህንነት ቀበቶ ማስተካከልና ማሰር፣ | 1 |
| 2 | **ሞተር ማስነሳት በሚመለከት** | |
| 2.1 | የሞተር ማስነሻ ቁልፍ አገባብ፣ | 1 |
| 2.2 | የሞተር ማስነሻ ቁልፍ አያያዝ፣ | 1 |
| 2.3 | ሞተር ማስነሳት | 1 |
| 2.4 | ዳሽ ቦርድ ምልከታ | 1 |
| 3 | **ጉዞ አጀማመር እና ጉዞን በሚመለከት** | |
| 3.1 | መነሻ ማርሽ አገባብ፣ | 2 |
| 3.2 | የእጅ ፍሬን አለቃቀቅና የእግር ፍሬን አያያዝ | 1 |
| 3.3 | መሪ አያያዝ | 1 |
| 3.4 | መስታወት ምልከታ | 1 |
| 3.5 | የምልክት አሰጣጥ/ፍሬቻና የእጅ ምልክት/፣ | 2 |
| 3.6 | ነዳጅን ከመነሻ ማርሽ ጋር አጣጥሞ ስለመነሳት፣ | 1 |
| 4 | **በተለያዩ የመንገድና ትራፊክ ሁኔታዎች ላይ የአነዳድ ባህሪ በተመለከተ** | |
| 4.1 | ረድፍ አጠባበቁ፣ | 3 |
| 4.2 | ረድፍ አለዋወጡ | 3 |
| 4.3 | መቅደምና ማስቀደም፣ | 3 |
| 4.4 | መስታወትና ፍሬን አጠቃቀም፣ | 1 |
| 4.5 | ፍጥነቱ፣ | 2 |
| 4.6 | ርቀት ጠብቆ ማሽከርከር፣ | 3 |
| 4.7 | ምልክት፣ መብራት፣ መስመር አጠቃቀም፣ | 2 |
| 4.8 | የፍሪሲዮን አጠቃቀም፣ | 2 |

| | | |
|---|---|---|
| 4.9 | የነዳጅ መስጫ ፔዳል አጠቃቀም፣ | 2 |
| 4.10 | ማርሽ አጨማመርና አቀናነስ በተለያየ የመንገድ ሁኔታ ፣ | 4 |
| 4.11 | የፍሬን አጠቃቀም፣ | 3 |
| 4.12 | የመሪ አጠቃቀም፣ | 3 |
| 4.13 | ዕይታና ምልከታ (Observation) ጥንቃቄ፣ | 3 |
| 4.14 | ለእግረኛና ለሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ቅድሚያ መስጠት በሚመለከት፣ | 2 |
| 4.15 | ወደግራና ወደቀኝ አዟዟሩ፣ | 3 |
| 4.16 | የኋላ ሚዛን አጠባበቅ፣ | 3 |
| 4.17 | የኋላ አነዳድ በቀጥታና በኩርባ መንገድ | 3 |
| 4.18 | በመስቀለኛና በመገናኛ፣ በባቡር ሃዲድ ስለማቋረጥና ስለመተላለፍ፣ | 3 |
| 4.19 | ዞሮ ስለመመለስ 'U' turn | 3 |
| 4.20 | የአደባባይ አዟዟርና ጥንቃቄ፣ | 3 |
| **5.** | **የመሰናክል ፈተና** | |
| 5.1 | የአንድ ቁጥር፣ አሰራር | 4 |
| 5.2 | የስምንት ቁጥር አሰራር | 10 |
| 5.3 | ጋራዥ አሰራር | 10 |
| 5.4 | ድልድይ አሰራር | 6 |
| | **ድምር** | **100%** |

## 8.3 የፈሳሽ$_1$፣የደረቅ$_2$፣ የህዝብ$_2$፣ የፈሳሽ$_2$ እና ደረቅ$_3$ ምድብ የተግባር ፈተና ቼክ ሊስት

| ተ.ቁ | የፈተና ይዘት | የተሰጠ ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | **ቅድመ ጉዞ በሚመለከት** | |
| 1.1 | አንድ አሽከርካሪ ተሽከርካሪውን ከማንቀሳቀሱ በፊት መፈተሽ የሚገባውን በተግባር ማሳየት | 2 |
| 1.2 | በር አከፋፈትና አዘጋግ /ጋቢና አገባብ/ | 1 |
| 1.3 | መቀመጫ ወንበር፣ መስታወት፣ የደህንነት ቀበቶ ማስተካከልና ማሰር | 1 |
| 2 | **ሞተር ማስነሳት በሚመለከት** | |
| 2.1 | የሞተር ማስነሻ ቁልፍ አገባብ፣ | 1 |
| 2.2 | የሞተር ማስነሻ ቁልፍ አዟዟር፣ | 1 |
| 2.3 | ሞተር ማነሳስ | 1 |
| 2.4 | ዳሽ ቦርድ ምልከታ | 1 |
| 3 | **ጉዞ አጀማመር እና በሚመለከት** | |
| 3.1 | መነሻ ማርሽ አገባብ፣ | 2 |
| 3.2 | የእጅ ፍሬን አለቃቀቅና የእግር ፍሬን አያያዝ | 1 |
| 3.3 | መሪ አያያዝ | 1 |
| 3.4 | መስታወት ምልከታ | 1 |
| 3.5 | የምልክት አሰጣጥ /ፍሬቻና የእጅ ምልክት/ | 2 |
| 3.6 | ነዳጅን ከመነሻ ማርሽ ጋር አጣጥሞ ስለመነሳት፣ | 1 |
| 4 | **በተለያዩ የመንገድና ትራፊክ ሁኔታዎች ላይ የአነዳድ ባህሪ በተመለከተ** | |
| 4.1 | ረድፍ አጠባበቁ፣ | 3 |
| 4.2 | ረድፍ አለዋወጡ | 3 |
| 4.3 | መቅደምና ማስቀደም፣ | 3 |
| 4.4 | መስታወትና ፍሬን አጠቃቀም፣ | 1 |
| 4.5 | ፍጥነቱ፣ | 2 |
| 4.6 | ርቀት ጠብቆ ማሽከርከር፣ | 2 |
| 4.7 | ምልክት፣ መብራት፣ መስመር አጠቃቀም፣ | 2 |
| 4.8 | የፍሪሲዮን አጠቃቀም፣ | 2 |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

| | | |
|---|---|---|
| 4.9 | የነዳጅ መስጫ ፔዳል አጠቃቀም፣ | 2 |
| 4.10 | ማርሽ አጨማመርና አቀናነስ በተለያየ የመንገድ ሁኔታ፣ | 4 |
| 4.11 | የፍሬን አጠቃቀም፣ | 3 |
| 4.12 | የመሪ አጠቃቀም፣ | 3 |
| 4.13 | ዕይታና ምልከታ (Observation) ጥንቃቄ፣ | 2 |
| 4.14 | ለእግረኛና ለሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ቅድሚያ መስጠት ብሚመለከት፣ | 2 |
| 4.15 | ወደግራና ወደቀኝ አዟዟሩ፣ | 4 |
| 4.16 | የኋላ ሚዛን አጠባበቅ፣ | 4 |
| 4.17 | የኋላ አነዳድ በቀጥታና በኩርባ መንገድ | 4 |
| 4.18 | በመስቀለኛና በመገናኛ፣ በባቡር ሃዲድ ስለማቋረጥና ስለመተላለፍ፣ | 2 |
| 4.19 | ዞሮ ስለመመለስ 'U' turn | 3 |
| 4.20 | የአደባባይ አዟዟርና ጥንቃቄ፣ | 3 |
| **5.** | **የመሰናክል ፈተና** | |
| 5.1 | የአንድ ቁጥር፣ አሰራር | 4 |
| 5.2 | የስምንት ቁጥር አሰራር | 10 |
| 5.3 | ጋራዥ አሰራር | 10 |
| 5.4 | ድልድይ አሰራር | 6 |
| | **ድምር** | **100%** |

## 9. <u>ከአንድ ምድብ ወደ ሌላ ምድብ ሲለውጡ የሚሰጡ ስልጠናዎች እና ፈተናዎች</u>

1. በአንድ ምድብ ውስጥ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚቀይር አሽከርካሪ ለከፍተኛ ተሽከርካሪ የተጨመረውን ስልጠና ሰዓት ዝርዝር አሰራሩ ተለይቶ በሰንጠረዥ-01 ተገልጿል፡፡
2. ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ አሽከርካሪ የሌላ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት ከፈለገ ለምድቡ የሚሰጠውን ልዩ የንድፈ-ሀሳብና የተግባር ስልጠና እና ፈተና መውሰድ እንዳለበት በአዋጅ 600/2000 አንቀጽ-7 ቁጥር-3 ተደንግጓል፡፡ ምድቦች የራሳቸው የሆነ ልዩ የንድፈ-ሀሳብ ስልጠና በስርዓተ-ትምህርቱ ላይ ተካቶላቸዋል፡፡ ስለዚህ አሽከርካሪዎች ከምድብ ምድብ ሲቀይሩ የሚሰጣቸው የንድፈ-ሀሳብ ስልጠና በስርዓተ-ትምህርቱ መሰረት በሰንጠረዥ -02

ተገልጿል፡፡ በተጨማሪ የተግባር ስልጠና ከአንድ ምድብ ወደ ሌላ ምድብ የተለያየ ስለሆነ ከዚያው ምድብ ተሽከርካሪ ክብደት በታች የሚሆን ንዑስ ምድብ ከተጠየቀ በሰንጠረዥ-03 እንደተገለጸው ሁለት ሰዓት የተግባር ስልጠና ወስዶ እንዲፈተን ነገር ግን ከዚያ ምድብ ተሽከርካሪ ክብደት በላይ ከጠየቀ ተጨማሪ ሰዓት ብቻ እንዲሰለጥን ሆኖ ሙሉ የስልጠናና የምዘና አሰጣጥ ስርዓት ተለይቶ በሰንጠረዥ-04 ተገልጿል፡፡

3. ማንኛውም የሞተር ሳይክል ፈቃድ የሚያወጣ አሽከርካሪ በምድቡ ከተሰጠው የተግባር ስልጠና ውስጥ 5 ሰዓት በባለ ሶስት እግር ሞተር ሳይክል እና ቀሪውን 10 ሰዓት በባለ ሁለት እግር ሞተር ሳይክል ሰልጥነው የተግባር ምዘናውን በባለ ሁለት እግር ሞተር ሳይክል መውሰድ አለበት፡፡
4. ከአንድ ምድብ ወደ ሌላ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መቀየር የሚቻለዉ ለምድቡ የተቀመጠዉ የጤና ምርመራ፣ የትምህርት ደረጃና የዕድሜ ገደብ የተሟላ ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡

## 10 በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ማሽከርከር የሚቻለዉ ከዚህ በታች በተዘረዘረው ስንጠረዥ መሰረት ነዉ፡፡

| የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ምድብ | | ለማንቀሳቀስ የሚያስችለው ተሽከርካሪ |
|---|---|---|
| የሞተር ሳይክል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ምድብ፡ ሞ | | - በሞተር ተሽከርካሪ ፍቃድ ማረጋገጫ ባለሁለት እግር ሞተር<br>- ከታክሲ አገልግሎት ውጪ ባለ ሶስት እግር የሆነ ሞተር ተሽከርካሪ |
| ታክሲ አንድ ምድብ-- ታ1 | | - በታክሲ አገልግሎት የተመዘገበ ባለ ሶስት እግር የሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ |
| አዉቶሞቢል ምድብ-- አ | | - እስከ 12 መቀመጫ ያለዉ ማንኛዉም ዓይነት የግል አዉቶሞቢል፡፡ |
| | | - በግል ንግድ የተመዘገበ አሽከርካሪውን ጨምሮ እስከ 5 መቀመጫ ያለው ተሽከርካሪ |
| | | - እስከ 5 መቀመጫ ያለው ድርብ ተግባር የሚል በሊብሬው ላይ የተመዘገበ |
| | | - በንግድ ያልተመዘገቡ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሽከርካሪውን ጨምሮ እስከ 12 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎችን፡፡ |
| | | - ለማስተማሪያነት በማሰልጠኛ ተቋሙ ስም የተመዘገበ ተሽከርካሪ እስከ 12 መቀመጫ ያላቸው |
| ታክሲ ሁለት ምድብ-- ታ2 | | - በአዉቶሞቢል የተመዘገቡትን በሙሉ ማሽከርከር ይቻላል፡፡<br>- በታክሲ አገልግሎት ተመዝግበዉ እስከ 12 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎችን ማሽከርከር የሚችሉ ሲሆን ነገር ግን ባለሶስት እግር ተሽከርካሪን ማሽከርከር አይችልም፡፡ |
| የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የአሽ/ብ/ማረጋገጫ | ምድብ-- ደ1 | - በሊብሬው ላይ ለደረቅ ጭነት አገልግሎት ተመዝግቦ ጠቅላላ ክብደቱ እስከ 7000 ኪ.ግ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን፡፡<br>- በመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በደረቅ ጭነት አገልግሎት እስከ 7000 ኪ.ግ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን፡፡ |
| | ምድብ- ደ2 | - በደረቅ 1 ማሽከርከር የተፈቀዱትን በሙሉ ማሽከርከር ይችላል፡፡<br>- በሊብሬው ላይ ለደረቅ ጭነት አገልግሎት የተመዘገበ ጠቅላላ ክብደቱ እስከ 28 000 ኪ.ግ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ያለተሳቢ፡፡<br>- በመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አገልግሎት ተመዝግበው በደረቅ ጭነት አገልግሎት እስከ 28 000 ኪ.ግ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ያለተሳቢ፡፡ |
| | ምድብ- ደ3 | - በደረቅ 1 እና በደረቅ 2 ማሽከርከር የተፈቀዱትን በሙሉ ማሽከርከር ይችላል፡፡<br>- በሊብሬው ላይ ለደረቅ ጭነት አገልግሎት የተመዘገበ ማንኛውም ዓይነት የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከተሳቢ ጋር ወይም ሎቤድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ተሽርካሪዎችን<br>- በመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አገልግሎት የተመዘገበ ማንኛውም ዓይነት የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከተሳቢ ጋር ወይም ሎቤድ ተሽከርካሪዎችን |
| | የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የአሽ/ብ/ማረጋገጫ | ምድብ-ህ1 | - በህዝብ ማመላለሻና በንግድ አገልግሎት የተመዘገቡ አሽከርካሪውን ጨምሮ እስከ 25 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎችን::<br>- መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ተመዝግቦ አሽከርካሪውን ጨምሮ እስከ 25 መቀመጫ ያላቸውን በህዝብ አገልግሎት የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን:: |
| | | ምድብ-ህ2 | - በህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የተመዘገቡ ማንኛውም የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ<br>- በህዝብ 1 ማሽከርከር የተፈቀዱትን በሙሉ ማሽከርከር ይችላል::<br>- መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አገልግሎት የተመዘገቡ ማንኛውም ዓይነት የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን:: |
| ፩ | ለፈሳሽ አገልግሎት የተመዘገበ | ምድብ-ፈ1 | - በፈሳሽ አገልግሎት ተመዝግቦ እስከ 18 000 ሊትር የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ያለ ተሳቢ |
| | | ምድብ-ፈ2 | - ማንኛውም ዓይነት የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከሙሉ ወይም ከግማሽ ተሳቢ ጋር ወይም ሎቤድ |

## 11.መረጃና ሪፖርት ስለመላክ

1. የትራንስፖርት ቢሮዎች በክልሉ የተሰጡና የፈቃድ ሰጪ አካላት የሰጧቸውን የአሽከርካሪዎች ስም ዝርዝር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በየሶስት ወሩ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት ማደረግ አለባቸው::
2. የትራንስፖርት ቢሮዎች የእያንዳንዱን የፈቃድ ሰጪ አካልና የማሰልጠኛ ተቋም አፈጻጸም እየገመገመ በየሶስት ወሩ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት ማደረግ አለባቸው::

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## 12.የሽግግር ጊዜ አሰራር መመሪያ

1. አዲሱ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በማዕከል እስኪ.ታተም ድረስ በክልል የሚሰጠው ፈቃድ ለአንድ ዓመት ብቻ የሚያገለግል መሆን አለበት፡፡ ይህ መመሪያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በስታንዳርድ መሰረት መሆን አለበት፡፡
2. የተግባር ፈተና መፈተኛ የትራፊክ ኮምፕሌክስ የሌለው የፈቃድ ሰጪ አካል እውቅና ፈቃድ በወሰደ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ የተሟላ የትራፊክ ኮምፕሌክስ ማዘጋጀት አለበት እስከዚያ ድረስ ግን የፈተና ስርአቱ የሚሆነው የትራፊክ ፍሰት በበዛባቸውና ክልሉ በእርግጠኝነት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የትራፊክ ኮምፕሌክስ ለመገንባት ዕቅድ በያዘላቸው ከተሞች የተግባር ፈተና መፈተን አለበት፡፡
3. የተግባር ፈተና ለመፈተን የሴኩሪቲ ካሜራ የሌላቸው የፈቃድ ሰጪ አካላት በቪዲዮ ካሜራ የታገዘ የተግባር ፈተና መፈተን አለባቸው፡፡

## 13. በፍርድ ቤት የተለወጠ ስም ስለመተካት

የፍርድ ቤት ውሳኔ የያዘ ደብዳቤ (የደብዳቤው ኦርጅናልና ፎቶ ኮፒ) ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 14. ስለጠፋ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ወይም ግልባጭ ስለመስጠት

1. አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በአካል መታወቂያ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡
2. አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በትክክል መጥፋቱን ከፖሊስ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
3. የአገልግሎት ክፍያ የሚከፍለው የእድሳት ጊዜ ገደቡ አለማለፉን ከተረጋገጠ በኂላ ብቻ መሆን አለበት፡፡
4. ፈቃድ ሰጪው አካል የጠፉ ፈቃዶችን በመረጃ መረብ ወይም በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ዋጋ እንደሌላቸው ማሳወቅ አለበት፡፡
5. አንድ ጊዜ የጠፋበትና ግልባጭ የወሰደ አሽከርካሪ ለሁለተኛ ጊዜ ከጠፋበት መውሰድ የሚችለው መጀመሪያ ጠፍቶበት ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ 3/ሶስት/ ወር ሲሞላው ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በዓመቱ ውስጥ ከ3/ሶስት/ ጊዜ በላይ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከወሰደ ለ6/ስድስት/ ወር ይታገዳል፡፡
6. የዕድሳት ጊዜ ገደብ ያለፈበት አሽከርካሪ የመፈተኛ ተሽከርካሪ ራሱ አቅርቦ የተግባር ፈተና ይወስዳል፡፡ ሆኖም በደረጃው የሚፈቅደው ተሽከርካሪ በግሉ የተመዘገበ ወይም በሚያገለግለው ተቋም የተመዘገበና የቴክኒክ ብቃት መሆን አለበት፡፡



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## 15. የክልሎችና የቅ/መ/ቤቶች ትራንስፖርት ቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት፡፡

15.1 አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ መመሪያና መስፈርቶች ላይ ያሉ የአሰራርና የአተገባበር ክፍተቶችን መከታተልና የማሻሻያ ሀሳብ ለባለስልጣኑ ማቅረብ፡፡

15.2 ፈቃድ ሰጪ አካላትና ማሰልጠኛ ተቋማትን ባለስልጣኑ ባወጣው መስፈርቱ ማደራጀትና ስልጠና እና ፈተና እንዲሰጡ በባለስልጣኑ ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

15.3 ፈቃድ ሰጪ አካላትና ማሰልጠኛ ተቋማት በወጣው አዋጅ፣ መመሪያና መስፈርት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል፣ መደገፍና መቆጣጠር፡፡

15.4 የፈቃድ ሰጪ አካላት የሰጧቸውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረገገጫ ፈቃዶች ዝርዝር ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ፡፡

15.5 የፈቃድ ሰጪውንና የተቋማትን አፈጻጸም እየገመገሙ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ፡፡

15.6 ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ወደ ማሰልጠኛ ተቋማትና ፈቃድ ሰጪ አካላት ማውረድ

## 16. የፈቃድ ሰጪ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1. ባለስልጣኑ ባዘጋጀው መስፈርት መሰረት ማደራጀት
2. አፈጻጸማቸውን ለክልል ቢሮው ሪፖርት ማድረግ
3. ማሰልጠኛ ተቋማትን መቆጣጠር
4. መስፈርት አሟልተው የተገኙ እጩ አሽከርካሪዎችን ብቻ አጣርቶ መፈተን
5. የጽሑፍና የተግባር ፈተና በተከታታይ መፈተን
6. የፈታኝ ባለሙያዎችን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ማሟላት
7. ያልሰለጠነ አሽከርካሪ እንዳይፈተን መቆጣጠር
8. ባለስልጣኑ ባወጣው ይዘት፣ ቅርጽና ጥራት መሰረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት፡፡
9. በፈተና ላይ ያሉ ብልሹ አሰራሮችን መከታተልና ማስወገድ
10. ለተቋማትና አሽከርካሪዎች ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፡፡
11. የማሰልጠኛ ተቋማትን በየጊዜው አፈጻጸማቸውን መገምገምና የዕርምት ዕርምጃ መውሰድ፡፡

## ሰንጠረዥ - 01 - በአንድ ምድብ ውስጥ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ሲቀየር የሚሰጡ የተግባር ስልጠና ሰዓቶች።

| ተ.ቁ | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | የኮርስ ዓይነት | የስልጠና ሰዓት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ቲዮሪ | ተግባር |
| 1 | ታክሲ$_1$ | ታክሲ$_2$ | የማሽከርከር ስልት | - | 25 |
| 2 | ህዝብ$_1$ | ህዝብ$_2$ | የማሽከርከር ስልት | - | 15 |
| 3 | ደረቅ$_1$ | ደረቅ$_2$ | የማሽከርከር ስልት | - | 15 |
| 4 | ደረቅ$_1$ | ደረቅ$_3$ | የማሽከርከር ስልት | - | 30 |
| 5 | ደረቅ$_2$ | ደረቅ$_3$ | የማሽከርከር ስልት | - | 15 |
| 6 | ፈሳሽ$_1$ | ፈሳሽ$_2$ | የማሽከርከር ስልት | - | 15 |

## ሰንጠረዥ -02 - ከምድብ ምድብ ሲለወጥ የሚሰጡ የንድፈ-ሀሳብ ስልጠና ይዘቶች እና ሰዓቶች

| ከማንኛውም ምድብ ከታች ወደ ተጠቀሱት ምድቦች ሲቀየር | የስልጠና ይዘት | የልዩ የስልጠና ሰዓት | |
|---|---|---|---|
| | | ቲዎሪ | የልዩ ስልጠና የቲወሪ ስርቶ ማሳያ |
| ደ$_1$, ደ$_2$, ደ$_3$ | የደረቅ ጭነት አጫጫንና አወራረድ | 5 | 2 |
| ህ$_1$, ህ$_2$, ታ$_1$, ታ$_2$ | ከተሳፋሪዎችና ከስራ ባልደረባ ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር | 4 | |
| | ተሳፋሪዎችን በትህትና መያዝና ደህንነት መጠበቅ | 4 | |
| ፈ$_1$ ,ፈ$_2$ | የፈሳሽ ጭነት አጫጫንና አወራረድ | 3 | 2 |

## ሰንጠረዥ - 03 - ከምድብ ምድብ ሲለወጥ የሚሰጡ የተግባር ስልጠና ሰዓቶች

| ተ.ቁ | ከ --- ምድብ | ወደ --- ምድብ | የተግባር አነዳድ ስልጠና ሰዓት |
|---|---|---|---|
| 1 | ዶ$_1$, ዶ$_2$, ዶ$_3$ , ፊ$_1$ ,ፊ$_2$ | ታ$_2$ | 2 |
| 2 | ሀ$_1$, ፊ$_1$,ፊ$_2$ , ሀ$_2$ | ዶ$_1$ | 2 |
| 3 | ፊ$_2$ , ሀ$_2$ | ዶ$_2$ | 2 |
| 4 | ዶ$_2$ , ዶ$_3$ , ሀ$_2$ ሀ$_1$ | ፊ$_1$ | 2 |
| 5 | ዶ$_2$ , ዶ$_3$ ,ፊ$_1$ ,ፊ$_2$ | ሀ$_1$ | 2 |
| 6 | ዶ$_3$‹ ሀ2 | ፊ$_2$ | 2 |
| 7 | ዶ$_3$, ፊ$_2$ | ሀ$_2$ | 2 |

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport Authority No. 1

## ሰንጠረዥ - 04 - ከምድብ ምድብ ሲለወጥ የሚሰጡ የተግባር ስልጠና ሰዓቶች

| ተ.ቁ | ከታች ከተጠቀሱት ምድቦች | ወደ ታች ወደተጠቀሱት ምድቦች ሲለወጥ | ከሁለተኛ ኮለመን ወደ ሦስተኛ ኮለመን ሲለወጥ የሚሰጥ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሞተር ሳይክል | ሌሎች ካታጐሪዎች ከታ1 በስተቀር | የየምድቡን ሙሉ ሰዓት |
| 2 | ሞተር ሳይክል | ታክሲ 1 | 5 |
| 3 | ታክሲ$_1$ | ሞተር ሳይክል | 5 |
| 4 | ከ ታ$_1$፣ በስተቀር ሌሎች ምድቦች | ሞተር ሳይክል | 15 |
| 5 | ከሞተር ሳይክል በስተቀር ሌሎች ምድቦች | ታክሲ$_1$ | 15 |
| 6 | አዉቶሞቢል | ታክሲ 2 | 5 |
| 7 | ታክሲ$_1$ | ሌሎች ምድቦች (ከሞተር ሳይክል በስተቀር) | የየምድቡን ሙሉ ሰዓት |
| 8 | አውቶሞቢል | ህዝብ$_1$ | 15 |
| 9 | አውቶሞቢል | ህዝብ$_2$ | 30 |
| 10 | አውቶሞቢል | ደረቅ$_1$ | 15 |
| 11 | አውቶሞቢል | ደረቅ$_2$ | 25 |
| 12 | አውቶሞቢል | ደረቅ$_3$ | 35 |
| 13 | አውቶሞቢል | ፈሳሽ$_1$ | 25 |
| 14 | አውቶሞቢል | ፈሳሽ$_2$ | 35 |
| 15 | ታክሲ$_2$ | ህዝብ$_1$ | 10 |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Transport Authority No. 1

| ተ.ቁ | ከታች ከተጠቀሱት ምድቦች | ወደ ታች ከተጠቀሱት ምድቦች ሲለወጥ | ከሁለተኛ ኮለመን ወደ ሦስተኛ ኮለመን ሲለወጥ የሚሰጥ |
|---|---|---|---|
| 16 | ታክሲ$_2$ | ህዝብ$_2$ | 25 |
| 17 | ታክሲ$_2$ | ደረቅ$_1$ | 10 |
| 18 | ታክሲ$_2$ | ደረቅ$_2$ | 20 |
| 19 | ታክሲ$_2$ | ደረቅ$_3$ | 30 |
| 20 | ታክሲ$_2$ | ፈሳሽ$_1$ | 20 |
| 21 | ታክሲ$_2$ | ፈሳሽ$_2$ | 30 |
| 22 | ደረቅ$_1$ | ህዝብ$_1$ | 5 |
| 23 | ደረቅ$_1$ | ፈሳሽ$_1$ | 10 |
| 24 | ደረቅ$_1$ | ህዝብ$_2$ | 15 |
| 25 | ደረቅ$_1$ | ፈሳሽ$_2$ | 20 |
| 26 | ህዝብ$_1$ | ደረቅ$_3$ | 20 |
| 27 | ህዝብ$_1$ | ፈሳሽ$_2$ | 20 |
| 28 | ህዝብ$_2$ | ደረቅ$_3$ | 10 |
| 29 | ደረቅ$_2$ | ህዝብ$_2$ | 5 |
| 30 | ፈሳሽ$_1$ | ህዝብ$_2$ | 10 |
| 31 | ፈሳሽ$_1$ | ደረቅ$_2$ | 5 |
| 32 | ፈሳሽ$_1$ | ደረቅ$_3$ | 10 |
| 33 | ፈሳሽ$_2$ | ደረቅ$_3$ | 5 |
| 34 | ደረቅ$_2$ | ፈሳሽ$_2$ | 10 |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

ሰንጠረዥ - 05 - ከሌሎች ምድቦች ወደ አውቶሞቢል እና ታክሲ ሁለት ምድብ የሚቀየሩ

| ተ.ቁ | ከ-ምድብ | ወደ- ምድብ | የፈተና ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 1. | ደረቅ$_1$ ፣ ደረቅ$_2$ ፣ ደረቅ$_3$ ፣ ህዝብ$_1$ ህዝብ$_2$ ፣ ፈሳሽ$_1$ ፣ ፈሳሽ$_2$ | አውቶሞቢል | የተግባር ፈተና ብቻ |
| 2. | ታክሲ $_2$ ፣ | አውቶሞቢል | ያለምንም ስልጠናና ፈተና ማግኘት ይችላል |
| 3. | ህዝብ$_1$ እና ህዝብ$_2$ | ታክሲ $_2$ እና አውቶሞቢል | የተግባር ፈተና ብቻ |

## የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት መስፈርት (Standards)

የትራንስፖርት ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 600/2000 አንቀጽ 9/1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማሠልጠኛ ተቋማትን መስፈርት አውጥቷል:: ስለዚህ ማሰልጠኛ ተቋም የሚያቋቁሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ባለሃብቶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የሚችሉት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ ነው ::

### I. የቢሮ አደረጃጀት

1. የተቋሙ ዳይሬክተር
2. የምዝገባና ገንዘብ ተቀባይ ሠራተኛ
3. የንድፈ ሃሳብና የተግባር አሰልጣኞች /የትራንስፖርት ቴክኒሽያኖች/
4. ሠራተኞች ከባለጉዳዩ ወይም ከሰልጣኙ ጋር እንዳይገናኙ ለማድረግ ግማሽ ባንኮኒ የሆነ መለያ መኖር አለበት::
5. ለሰልጣኝና ለባለጉዳዩ እንዲሁም ለሠራተኞቹ በቂ የሆነ የፕላስቲክ ወይም የጨርቅ ወንበር እና ጠረጴዛዎች ማዘጋጀት ያስፈልጋል ::
6. ለሰልጣኞች የስልጠና መታወቂያ ለመስጠት የዲጂታል ካሜራ ከነኮምፒዩተሩ መኖር አለበት ::

* የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ... በትራንስፖርት ... ባለሥልጣን ... Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1 *

## II. የማስተማሪያ ክፍሎች

1. ለአንድ ሰልጣኝ 1.2 ካሬ ሜትር ቦታ ታሳቢ በማድረግ የማስተማሪያ ክፍሎች መጠን 30 ካሬ ሜትር ሆኖ የተማላ ነጠላ ዴስክ፤ ጠረጴዛዎች፤ ወንበሮችና ፣ ነጭ ወይም ጥቁር ሰሌዳና ዳስተር ያላቸው፣ ድምጽ የማያስተጋቡ ሆኖ በአንድ ክፍል ውስጥ የሰልጣኝ ብዛት ከ 25 /ሃያ አምስት / መብለጥ የለበትም።
2. በቂ ብርሃንና ተስማሚ አየር የሚያስገቡ መስኮቶች ያሉትና ጣሪያቸው ከፍታው 2.50 እና ከዚያ በላይ የተሰሩ ክፍሎች
3. መምህራን ዕውቀታቸውን ለማዳበር እንዲችሉና በየጊዜው ከሚወጡት አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ፣ እንዲሁም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አውጪዎችም ሙያቸውን ለማሻሻልና ግንዛቤያቸውን ለማስፋት እንዲችሉ የስልጠና ማንዋሎችና መጽሐፍት ያሉት ቢያንስ 25 ሰልጣኝ ሊያስተናግድ የሚችል ቤተመፃሕፍት መኖር አለበት
4. እያንዳንዱ ተፈታኝ በኮምፒዩተር ላይ ማሰልጠን በሚችል መልኩ በሚገባ የተደራጀ አንድ የጽሁፍ ፈተና የኮምፒዩተር ማለማመጃ ክፍል ሊኖራቸዉ ይገባል።
5. የዕሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ።
6. የማስተማርና የመማር ሂደቱን የሚያደናቅፍ ጫጫታ የሌለው አካባቢ መሆን አለበት።
7. እንግዶች ጉዳያቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ ሳይሰለቹ እንዲቆዩ ለማድረግ አንድ ቴሌቪዥንና አንድ ቪዲዮ ዴክ ያስፈልጋል ።
8. የመፀዳጃ ክፍል ለወንድና ለሴት አንድ አንድ፣

## III ወርክሾፕ

- ሞተር ክፍል
- ሀይል አስተላላፊ ክፍል
- የመሪ ክፍል
- የፍሬን ክፍል
- የኤሌክትሪክ ክፍል
- የማቀዝቀዣ ክፍል
- የማለስለሻ ክፍል
- የነዳጅ ማስተላፊያ ክፍል

## IV. የማስተማሪያ ተሽከርካሪዎች ደረጃ /ስታንደርድ/

1. አንድ ማሰልጠኛ ተቋም ስልጠና ለመስጠት የፈቃድ ጥያቄ ሲያቀርብ ለማሰልጠን ጥያቄ ባቀረበዉ ምድብ ሁሉም የማስተማሪያ ተሽከርካሪዉ በተቋሙ ስም የተመዘገቡ መሆን አለበት
2. ቀደም ሲል ፍቃድ የተሰጣቸዉ ማሰልጠኛ ተቋማት ፈቃድ በተሰጣቸዉ ምድቦች ሁሉ የማስተማሪያ ተሽከርካሪዎችን በማሰልጠኛ ተቋሙ ስም የተመዘገበ መሆን አለባቸዉ::
3. ማንኛዉም ተሽከርካሪ ከአንድ ማሰልጠኛ ተቋም በስተቀር በሌላ ተቋማት እንዲሁም በቅርንጫፍ ተቋማት ተመዝግቦ አገልግሎት መስጠት አይችልም::
4. እያንዳንዱ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም በሚሰጠው የስልጠና ዓይነትና የአሽከረካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ቲዎሪን(ንድፍ ሃሳብን) ከተግባር ጋር አዋህዶ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ በቂ የሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ ተሽከርካሪዎችና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ከዚህ በታች በሰንጠረዡ በተመለከተው መሠረት እንዲኖሩት ያስፈልጋል ::

| ተ.ቁ. | የተሽከርካሪ ዓይነት | የአሽ/ብ/ቃ/ማ/ ፈቃድ ምድቦች | የማስተማሪያ ተሽከርካሪ ደረጃ | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሞተር ሳይክል | ሞ | ባለሁለት እግር ሞተር ብስክሌት ከ 125 ሲ.ሲ. እስከ 185 ሲ.ሲ. እና ባለሶስት እግር ሞተር ብስክሌት | አንድ ባለሁለት እግር ሞተር ሳይክልና አንድ ባለሶስት እግር ሞተር ሳይክል ሁለቱንም ሞተር ሳይክሎች ሊኖሩት ይገባል:: |
| 2 | አውቶሞቢል | አ | - ከ 8 እስከ 12 መቀመጫ ያለው ተሽከርካሪ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| 3 | ታክሲ | ታ -1 | ባለሶስት እግር ሞተር ሳይክል | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| | | ታ -2 | 12 መቀመጫ ያለው ሚኒባስ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| 4 | የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ | ህ-1 | 24 መቀመጫ ያለው ተሽከርካሪ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| | | ህ-2 | ከ55 እስከ 62 መቀመጫ ያለው ተሽከርካሪ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| 5 | የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ | ደ-1 | ጠቅላላ ክብደቱ ከ5.8ሺ--7ሺ ኪ.ግ. የሆነ የደረቅ ጭነት ተሽከረካሪ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| | | ደ-2 | ጠቅላላ ክብደቱ ከ18ሺ. - 28 ሺ. ኪ.ግ. የደረቅ ጭነት ተሽከረካሪ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| | | ደ-3 | ጠቅላላ ክብደቱ ከ25ሺ. - 28ሺ. ኪ.ግ. የደረቅ ጭነት ተሽከረካሪ ከከባድ ተሳቢ ጋር /ሉቤድ/ የሆነ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |

| ተ.ቁ | የተሽ/ዓይነት | የአሽ/ብ/ማ/ ፈቃድ ምድቦች | የማስተማሪያ ተሽከርካሪ ደረጃ | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 6 | የፈሳሽ ጭነት | ፈ-1 | - ከ12ሺ. እስከ 18ሺ. ሊትር የመጫን አቅም የለዉ የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| | | ፈ-2 | - ከ14ሺ. እስከ 18ሺ. ሊትር የመጫን አቅም የለዉ የፈሳሽ ጭነት ተሽከረካሪ ከከባድ ተሳቢ ጋር የሆነ | የሰልጣኝና የተሽከርካሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| 7 | ኮምፒዩተር | | | ቢ.ያንስ አምስት |
| 8 | ፕሮጀክተር | | OHP | በአንድ ክፍል አንድ |
| 9 | ዴክና ቴሌቪዥን | | - | በአንድ ክፍል አንድ |

## V. የሙያተኞች ተፈላጊ ችሎታ

### ሀ. የተቋሙ ዳይሬክተር

1. የትምህርት ዓይነት፡-

   1.1 በትምህርት አመራር

   1.2 በቢዝነስ ማናጅመንት

   1.3 በአውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ

   1.4 በመካኒካል ኢንጂነሪንግ

   1.5 ወይም በሌሎች የትምህርት ዘርፎች የተመረቀ በአመራር ቢያንስ 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው፣

2. የትምህርት ደረጃ

   1.1 ዲግሪና ከዚያ በላይ

   2.2 ከላይ በተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ዲፕሎማ ያለውና 4 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ፣

### ለ. የምዝገባና ገንዘብ ተቀባይ ሰራተኛ

1. የትምህርት ዓይነት

   1.1 ሴክሬተሪያል ሳይንስ

   1.2 ኮምፒዩተር ሳይንስ

   1.3 ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

   1.4 አካውንቲንግ

2. የትምህርት ደረጃ

   2.1 10+[1] 10+2 ሌቭል 2 ደረጃ 2 ሠርተፍኬት

   2.2 10ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀና የ2 ዓመት አግባብ ያለው ልምድ በመሠረታዊ የኮምፒዩተር ዕውቀት ያለው ፣

## ሐ. የአሽከርካሪዎች የንድፈ ሀሳብና የተግባር አሰልጣኝ

1. የትምህርት ዓይነት

   1.1 አውቶመካኒክ፤ አውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ

   1.2 ኢንጅን ሰርቪስ፤ ፓወር ትሬን፤ ሜካኒካል ኢንጅነሪንግ፤ አውቶኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮኒክስ

2. የትምህርት ደረጃ

   - ዲፕሎማ 12+2
   - 10+3 ያጠናቀቀ
   - ደረጃ 3 እና ደረጃ 4 እና ከዚያ በላይ

- በደረጃው የመንጃ ፈቃድ / የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ/ ያለው
- ለመማር ማስተማር ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን የማይችል የጤና ሁኔታ ማቅረብ ይችላል

3. ልዩ ሥልጠና

   - በደረጃው የትራንስፖርት ቴክኒሺያን (አፕሮቫል) ሠርተፍኬት ያለው፣

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጪ የመንግስት መ/ቤቶች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት

በአዋጅ ቁጥር 600/2001 ዓ.ም አንቀጽ 6/2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የትራንስፖርት ባለሥልጣን ለአሽከረካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጪ የመንግስት መ/ቤቶች ውቅና ለመስጠት ይህን መስፈርት አውጥቷል ። ስለዚህ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የአሽከረካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት ።

### I የንድፈ ሀሳብና ተግባር ሥልጠና በተመለከተ

1. ሥልጠናውን ለግል ማሠልጠኛ ተቋማት ፍቃድ መስጠት የሚቻል ሲሆን መስፈርቱን የሚያሟላ ተቋም ካልተገኘ ግን በመንግስት መስሪያ ቤቶች ሊሰጥ ይገባል ።
2. ሥልጠናውን በግል ማሠልጠኛ ተቋማት ሆነ በመንግስት መ/ቤት ከተሰጠ ባለሥልጣኑ ያወጣውን የማሠልጠኛ ተቋማት መስፈርት ማሟላት አለበት ።
3. የተግባር ሥልጠናውን የትራፊክ ምልክቶች፣ የትራፊክ መብራቶችንና የመንገድ ላይ ቅቦችን አሟልቶ በያዘ የትራፊክ ኮምኘሌክስ ውስጥ ሊከናወን ይገባል ።

### II የጽሁፍ ፈተናን በተመለከተ

1. የጽሑፍ ፈተና መፈተን የሚያስችሉ ቢያንስ 10 ኮምፒዩተሮች፣
2. ለጽሑፍ ፈተና ምዝገባ ለማካሄድ የሚያስችሉ ኮምፒዩተሮች፣
3. የጽሑፍ ፈተናውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሴኩሪቲ ካሜራ፣
4. የጽሑፍ ፈተና በብዛትና በጥራት በኮምፒዩተር ኘሮግራም ውስጥ መኖር አለበት፣
5. የጽሑፍ ፈተና ውጤት ኮምፒዩተሩ ራሱ ተፈታኙ ፈተናውን እንዳጠናቀቀ ማሳወቅ አለበት፣
6. የጽሑፍ ፈተና ውጤት ከጽሑፍ ፈተና ክፍል ወደ ውጤት ማጠናከሪያ ኮምፒዩተር አውቶማቲካሊ በመረጃ መረብ መተላለፍ አለበት፣
7. የጽሑፍ ፈተና የሚፈተኑ ተፈታኞች ዝርዝር በኮምፒዩተር መረብ ወደ ፈተና ክፍል መተላለፍ አለበት፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## III የተግባር አነዳድ ፈተናን በተመለከተ

1. የተግባር አነዳድ ፈተና እና የጽሑፍ ፈተና ቀጠሮ በአንድ ላይ ይሰጣል፣
2. የጽሑፍና የተግባር አነዳድ ፈተና በተከታታይ ይሰጣል፣
3. የመፈተኛ ኮምኘሌክሱ
    - 1.1. ሙሉ የትራፊክ ምልክት ያለው::
    - 1.2. የትራፊክ መብራት ያለው::
    - 1.3. የመንገድ ላይ ቅቦች ያለው::
    - 1.4. በሴኩሪቲ ካሜራ ቁጥጥር የሚደረግበት::
    - 1.5. ተሽከርካሪዎችን በመካከለኛና በከፍተኛ ፍጥነት መንዳት የሚያስችል የትራፊክ ፍሰት ያለው::
    - 1.6. ዳገትና ቁልቁለት የለው::
    - 1.7. መነሻና መድረሻውና የመሰናክል መፈተኛ ቦታ ያለው
    - 1.8. ለመሰናክል ፈተና ሙሉ ጉቶ ያለውና በ check list የተቀመጡትን ነገሮች መፈተን የሚያስችል::
4. የፈታኞች መቀመጫ ማማ ሊኖረው ይገባል :: ማማው ከዝናብና ከጸሐይ የሚከላከል መሆን አለበት ::
5. የመፈተኛ check list በግልጽ ለእያንዳንዱ ውጤት ተሰጥቶ መዘጋጀት አለበት

## የፈቃድ ሰጪ አካላት

### IV. የሙያተኞች ተፈላጊ ችሎታ

**1. የቡድን መሪ**

ሀ. የትምህርት ዓይነት

- አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ፤ መካኒካል ኢንጂነሪንግ ፤አውቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግ

ለ. የትምህርት ደረጃ

- ዲግሪ
- በደረጃው የመንጃ ፈቃድ / የአሽ /ብ/ማ/ ፈቃድ ያለው/
- በደረጃው የትራንስፖርት ቴክኒሺያን ሠርተፍኬት ያለው

**2. ፈታኝ ቴክኒሺያኖች**

ሀ. የትምህርት ዓይነት

- አውቶሞቲቭ

ለ. የትምህርት ደረጃ

- ዲኘሎማ፤ 12+2
- $10+^3$ ያጠናቀቀ
- ደረጃ 3 እና ደረጃ 4 እና ከዚያ በላይ
- በደረጃው የመንጃ ፈቃድ / የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ/
- በደረጃው የትራንስፖርት ቴክኒሺያን ሠርተፍኬት ያለው፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## 16. የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

በዚህ መመሪያ ተደራጅተዉ ፍቃድ የተሰጣቸዉ ተቋማት በመመሪያዉ አፈፃፀም ላይ ቅሬታ ሲኖራቸዉ ቅሬታቸዉን በየደረጃዉ አቅርበዉ እዲታይላቸዉ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

16.1 ቅሬታዉን በፅሁፍ አቅርቦ በ5 ቀን ዉስጥ ፍቃድ ሰጪ አካል መፍትሄ ይሰጣል፡፡

16.2 ፍቃድ ሰጪ አካል በተቀመጠዉ ጊዜ ገደብ መፍትሄ ካልሰጠ ወደ ክልል ትራንስፖርት መ/ቤት በመቅረብ እንዲታይለት ይደረጋል፡፡

16.3 በፍቃድ ሰጪውም ሆነ በክልል ትራንስፖርት መ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ ያልተስማማ ወይም ዉሳኔዉ ከህግና ከመመርያ አንፃር አግባብ አይደለም የሚል ቅሬታ አቅራቢ

16.4 በክልል ትራንስፖርት መ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ ያልተስማማ ወይም ዉሳኔዉ ከህግና ከመመርያ አንፃር አግባብ አይደለም የሚል ቅሬታ አቅራቢ ለትራንስፖርት ባለስልጣን ማቅረብ ይችላል፡፡ባለስልጣን መ/ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 17. ፍቃድ ስለማደስና አድራሻ ስለመቀየር

### ሀ. ፍቃድ ዕድሳት

17.1 ለተቋማት የሚሰጠዉ ፈቃድ የሚያገለግለዉ በፍቃድ ላይ በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ብቻ ነዉ፡፡

17.2. በተለያዩ ምክንያት በባለስልጣኑ ልዩ ዉሳኔ ካልሆነ በስተቀር ለተቋማት የሚሰጠዉ ፈቃድ ቢያንስ ለአንድ አመት ያገለግላል፡፡

17.3. ከፍቃድ ሰጪ ፈቃድ የተሰጠዉ ተቋም የፈቃድ ጊዜው እዳበቃ በ30 ቀናት ዉስጥ ቀርቦ ፍቃዱን ማሳደስ ግዴታ አለበት፡፡

17.4. ፍቃድ ሰጪው አካል የእድሳት ጥያቄዉ ሲቀርብለት አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታ

መሟላቱን አረጋግጦ በ15 ቀናት ዉስጥ ፈቃዱን ያድሳል፡፡

17.5 በዚህ መመርያ መሰረት በተቀመጠለት ጊዜ ዉስጥ ፈቃዱን ያላደሰ ተቋም በመመሪያዉ ላይ በተቀመጠዉ የቅጣት ደረጃ መሰረት አግባብ ያለዉ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## ለ. አድራሻ ስለመቀየር

1. ተቋማት በፍቃድ ሰጪው አካል ፍቃድ ያገኙበትን አድራሻ ሲቀይሩ በ1 (አንድ) ወር ጊዜ ዉስጥ ለፍቃድ ሰጪው አካል በፅሁፍ ማሳወቅ አለባቸዉ፡፡
2. ፍቃድ ሰጪው አካል በ15 ቀናት ጊዜ ዉስጥ አዲስ አድራሻ ለውጥን መመዘኛ ያሟላ መሆኑን በባለሙያዎች አረጋግጦ ለዉጡን በመቀበል አስፈላጊዉን የአድራሻ ማስተካከያ ያደርጋል፡፡
3. የአድራሻ ለዉጥ ሲያደርግ ለፍቃድ ሰጪው ያላሰወቀ ተቋም በዚህ መመርያ ዉስጥ በተቀመጠዉ መሰረት የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የዲሲፕሊን ቅጣቶች

## ሰንጠረዥ -06 በፈቃድ ሰጪ አካላት ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን ዕርምጃ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የሚወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ | እርምጃ የሚወስደው | እርምጃ መወሰዱን የሚከታተል |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ፈቃድ ሰጭ አካል የማሰልጠኛ ተቋማትን በሚገባና በመመሪያው መሰረት ካልተቆጣጠረ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 2 | የት/ደረጃ ጤና እና ዕድሜ ባልተሟሉበት ሁኔታ ፈቃድ ሰጪው አካል ፈትኖ ከተገኘ | 1. የመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ<br>- የመጨረሻ የጽሑፍማስጠንቀቂያ ለፈቃድ ሰጪው አካል ይሰጣል<br>- ተቋሙ ለአንድ ወር ይዘጋል<br>2.ለሁለተኛ ጊዜ የተሰጠው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰረዛል | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 3 | የጽሁፍ ፈተናን በተመለከተ መስፈርቱ ላይ በተቀመጡት መሰረት ያላሟላና ያልተደራጀ ሆኖ ሲፈተን የተገኘፈቃድ ሰጪ አካል | 1. የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 4 | የጽሑፍና የተግባር ፈተና በተከታታይ የማይሰጥ ሆኖ የተገኘፈቃድ ሰጪው አካል | 1. የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 5 | የተግባር ፈተናን በተመለከተ መስፈርቱ ላይ በተቀመጡት ነጥቦች መሰረት ያላሟላና ያልተደራጀ ሆኖ ሲሰራ ከተገኘፈቃድ ሰጪው አካል | 1.የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ<br>4. | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 6 | የሙያተኞች ተፈላጊ ችሎታን በተመለከተ ፈታኝ ቴክኒሺያኖች | 1. የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አውቶ ዲፕሎማና አፕሩቫል የሌላቸው እና ያለደረጃቸው ሲፈትኑ ከተገኙ | 2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ለ1 ዓመት እገዳ | | |
| 7 | በመስፈርቱ መሰረት ላልተደራጁ ተቋም ፈቃድ ሰጥቶ የተገኘፈቃድ ሰጪው አካል | 1.የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2.ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር ይታገዳል<br>3.ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 8 | ስልጠና ያልተሰጠው ወይም ስልጠናው በአግባቡ ያልጨረሰ ን ሰልጣኝ ፈትኖ የተገኘፈቃድ ሰጪው አካል | 1.የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2.ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3.ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 9 | የሚሰጠው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ባለስልጣኑ ካወጣው ደዘት፣ ቅርጽና ጥራት ውጭ ሲሰራ የተገኘፈቃድ ሰጪው አካል | 1.የመጀሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2.ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3..ለሶስተኛ ጊዜ ለ1 ዓመት እገዳ<br>4.ለአራተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 10 | በፈተና አሰጣጥ ላይ ብልሹ አሰራር ሲፈጽም የተገኘፈቃድ ሰጪው አካል | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ<br>- ለፈቃድ ሰጪው አካል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>- ለተፈታኙ ፈቃዱ የሰረዛል<br>- የዞኑ ሰራተኛ እርምጃ ይወሰድበታል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እገዳ<br>3. ለሶተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 11 | ተቋማትንና አሽከርካሪዎችን በማጉላላት ተደጋጋሚ ቅሬታ የተገኘበትፈቃድ ሰጪው አካል | 1. የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር ይታገዳል<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |
| 12 | ሰልጣኙ ብቃውን ማሽከርከር እየቻለ ለፈተና ላለማቅረብ ማጉላላት | 4. የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>5. ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር ይታገዳል<br>6. ለሶስተኛ ጊዜ ፈቃዱን መሰረዝ | የክልል ቢሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## ሰንጠረዥ-07 በማሠልጠኛ ተቋማት ላይ የሚወሰድ የዲሲኘሊን እርምጃ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የሚወሰደው የዲስፕሊን እርምጃ |
|---|---|---|
| 1 | ፍቃድ እንዲያገኝ ያስቻሉትን የመማር ማስተማር መስፈርቶችን ማለትም የመማሪያ ክፍሎች፣ የማሰልጠኛ ተሽከርካሪዎች መምህራኖች፣ የማስተማሪያ ማተሪያሎች ወዘተ አጓድሎ የተገኘ | 1. በአንድ ወር ጊዜ እንዲያስተካክል የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2. በ2ኛ ጊዜ ለ1 ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ<br>3. በ3ኛ ጊዜ የሥራ ፈቃዱን ማሰረዝና ተቋሙን መዝጋት |
| 2 | ▶ በተወሰነውና በተሰጠው ስርዓተ ትምህርት (ካሪኩለም) ጠብቆ የማያሰለጥን<br>▶ የወጣውን ስርአተ ትምህርት ጠብቆ ስልጠና ያልሰጠና የስልጠና መርሀ ግብር አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2. ለ2ኛ ጊዜ ለአንድ ዙር ስልጣኝ እንዳይቀበል ማገድ።<br>3. በ3ኛ ጊዜ ፈቃዱ ይሰረዛል ተቋሙ ይዘጋል። |
| 3 | ▶ ተወስኖ ከተሰጠው ቦታና ሰዓት ውጪ ተግባር ስልጠና ሲሰጥ የተገኘ<br>▶ የቴክኒክ ብቃቱ ባልተሟላ ተሽከርካሪ ስልጠና የሰጠ ወይም ለፈተና አቅርቦ ፈተናው እንዲስተጓጎል ያደረገ<br>▶ ማሰልጠኛ ተቋሙ ካስመዘገበው የማሰልጠኛ ተሽከርካሪ ውጭ ሲያሰለጥን የተገኘ<br>▶ እስቲከር በተሽከርካሪው ጎን ላይ ያለጠፈ እና ለማጅ የሚል ፁሁፍ በግልጽ ያላሳየ ተሽከርካሪ | 1. ለተቋሙ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት<br>2. ለ2ኛ ጊዜ ለ1 ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ።<br>3. በ3ኛ ደረጃ ጥፋቱን ፈፅመው ቢገኙ ተቋሙ ለ1ዓመት ይታገዳል።<br>4. በ4ኛ ደረጃ ጥፋቱን ፈፅመው ቢገኙ የተቋሙን ፈቃድ መሰረዝ። |
| 4 | ለአሽከርካሪነት ለመሰልጠን የተሰጡትን መስፈርቶች የማያሟሉት ሲያሰለጥን የተገኘ ማለት እድሜ፣ የጤና ሁኔታ የትምህርት ደረጃ …ወዘተ | 1. ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ አንድ ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ።<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ የተሰጠውን ፍቃድ ይሰረዝበታል። |
| 5 | ▶ የሰልጣኙን ሰዓት በመቀነስ ለግል ጥቅሙ ያዋለ ተቋም<br>▶ ብቃት የሌለውን ሰልጣኝ ብቃት አለው ብሎ ለፈተና ያቀረበ ተቋም<br>▶ የተሰጠውን የስልጠና ሰዓት አጠናቆ ብቃት ያለውን ሰልጣኝ ብቃት የለህም በማለት ከግል ፍላጎትና ጥቅሙ አንፃር ሰልጣኙን የሚያጉላላ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት።<br>2. በ2ኛ ደረጃ ለ1ኛ ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ።<br>3. በ3ኛ ደረጃ የተቋሙና የአሰልጣኙ ፈቃድ መሰረዝ። |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

| | | |
|---|---|---|
| | ▶ ሰልጣኙ ሳያውቀው እንደሰለጠነ አስመስሎ በመፈረም ያቀረበ ተቋም | |
| 6 | በማሰልጠኛ ተቋም ግቢ ውስጥ ለመማር ማስተማር የስራ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን አካላት ማለትም (አሰልጣኞች፡ ሰልጣኞች፡ የስራ መሪዎችንና ሌሎች ሰራተኞች) ማንኛውም የአልኮል መጠጥና አደንዛዥ እፅ ተጠቅሞ ከተገኘ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. በሁለተኛ ደረጃ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. በሶስተኛ ደረጃ የተቋሙ ፈቃድ መሰረዝ፡፡ |
| 7 | ከማሰልጠኛው ተቋም አቅም በላይ የሰልጣኝ ብዛት·ተቀብሎ ሲያሰለጥን የተገኘ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. በሁለተኛ ደረጃ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. በሶስተኛ ደረጃ የተቋሙ ፈቃድ መሰረዝ፡፡ |
| 8 | የስልጠና ሰዓት፡ የሰልጣኝ መብትና ግዴታ በግልጽ በቦርድ ያላሳወቀ | 1. በመጀመሪያ ጊዜ የእርምት የቃል ማስተንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡<br>2. በሁለተኛ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡<br>3. በሶስተኛ ጊዜ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ይታገዳል፡፡<br>4. በአራተኛ ጊዜ የተቋሙን ፈቃድ ይሰረዛል፡፡ |
| 9 | ▶ የሰልጣኞችን የምዝገባ ሰነዶች አቴንዳንስና የስልጠና መከታተያ ቅጽ<br>በአግባቡ አደራጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ፡፡<br>▶ ሰልጣኞች ስልጠና የሚጀምሩበትንና የሚያጠናቅቁበትን የጊዜ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ቦርድ ላይ ያለጠፈ፡<br>▶ አሰልጣኞችና ሰልጣኞችን መታወቂያ ወይም ባጅ እንዲያደርጉ ያላደረገ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. በሁለተኛ ደረጃ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. በሶስተኛ ደረጃ የተቋሙ ፈቃድ መሰረዝ፡፡ |
| 10 | አዲስ የሚቀበላቸውን ሰልጣኞች ዝርዝር ስልጠና ከመጀመሩ በፊት ለፍቃድ ሰጪው ሪፖርት ያላደረገ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. በሁለተኛ ደረጃ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. በሶስተኛ ደረጃ የተቋሙ ፈቃድ መሰረዝ፡፡ |
| 11 | ▶ ብቻውን ማሽከርከር የማይችል ተፈታኝ ለፈተና ያቀረበ፡<br>▶ ሰልጣኙ በቂ የኮምፒዩተር የልምምድ ፈተና ሳያደርግ ለፈተና ያቀረበ፡ | 2. በመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>3. በሁለተኛ ጊዜ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>4. በሶስተኛ ጊዜ ለ2ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>5. በአራተኛ ጊዜ የተቋሙ ፍቃድ ይሰረዛል፡፡ |
| 12 | ብቻውን ማሽከርከር እየቻለ ለፈተና አላቀርብም ብሎ ተፈታኙን ያጉላላ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. በሁለተኛ ደረጃ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. በሶስተኛ ደረጃ የተቋሙ ፈቃድ መሰረዝ፡፡ |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

| | | |
|---|---|---|
| | | |
| 13 | ► ለፍቃድ ሰጪ አካል ሳያሳውቅ የሰልጣኝ ለውጥ ያደረገ፡<br>► አሰልጣኞች ከተሰጣቸው የተሽከርካሪ ምድብ (የአፕሮቫል ደረጃ) ውጭ መድቦ ሲያሰለጥን የተገኘ<br>► ተሽከርካሪውን የማስተማሪያ ፈቃድለሌለው (በፈቃድ ሰጪው አካል በአሰልጣኝነት ላልመዘገበው) ሰው አሳልፎ በመስጠት ሲያሰለጥን የተገኘ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. በሁለተኛ ደረጃ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. በሶስተኛ ደረጃ የተቋሙ ፈቃድ መሰረዝ፡፡ |
| 14 | ► ለስልጠና አገልግሎት ክፍያ ህጋዊ ደረሰኝ ያልሰጠ<br>► ከሰልጣን በማታለል ገንዘብ የተቀበለ | 1. የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. በሁለተኛ ደረጃ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. በሶስተኛ ደረጃ የተቋሙ ፈቃድ መሰረዝ፡፡ |
| 15 | ► ተቋሙ በአንድ ዙር ለቲዎሪና ለተግባር ፈተና ካቀረባቸው ሰልጣኞች ከ30% በላይ የወደቀበት | 1. የመጀመሪያ የጽሁፍ ማስጠንቀቅያ መስጠት፡፡<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ፍቃዱን መሰረዝ ፡፡ |
| 16 | ► የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተቀመጠው የእደሳ ጊዜ ውስጥ ሳያሳድስ ሲሰራ የተገኘ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ሳምንትጊዜ ውስጥ እንዲያድስ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ፍቃዱን መሰረዝ ፡፡ |
| 17 | ► ለመ/ቤቱ ሳያሳውቅ ፈቃድ ያገኘበትን አድራሻ የቀየረ<br>► ለመ/ቤቱ ሳያሳውቅ ቅርንጫፍ ከፍቶ ሲሰራ የተገኘ | 1. ለ6 ወር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ከፈጸመ ፍቃዱን መሰረዝ፡፡ |
| 18 | ► በማሰልጠኛነት ያስመዘገበውን ተሽከርካሪ ለሌላ የንግድ አገልግሎት ያዋለ፡ | 1. የመጀመሪያ የጽሁፍ መስጠንቀቅያ መስጠት፡፡<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ተሽከርካሪው ከማሰልጠን ማገድ፡፡<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ የተቋሙን ፍቃድ መሰረዝ ፡፡ |
| 19 | ► ሰልጣኙን ከግል ፍላጎትና ጥቅም አንጻር ያጉላላ፡<br>► ተገቢውን ስልጠና ያጠናቀቀን ሰልጣኝ ለፈተና ሳያቀርብ ያጉላላ፡<br>► የሰልጣኞችን የፈተና ቀጠሮ ቅደም ተከተል በማዛባት አድሎ ያደረገ፡<br>► ለፈተና ማስቀጠሪያ በማለት ከተመኑ በላይ ከሰልጣኝ ክፍያ የተቀበለ፡ | 1. የመጀመሪያ የጽሁፍ መስጠንቀቅያ መስጠት፡፡<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ለ3ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>4. በአረራተኛ ጊዜ የተቋሙን ፍቃድ መሰረዝ ፡፡ |
| 20 | ► ለሰልጣኞች የፈተና ቀጠሮ (ፕሮግራም) ሳያሳውቅ የተገኘ ተቋም፡<br>► በፈተና አሰጣጥ ሂደት ላይ ሁከት ለመፍጠር የሞከረ ተቋም፡ | 1. የመጀመሪያ የጽሁፍ መስጠንቀቅያ መስጠት፡፡<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ለ1ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>3. ለሶስተኛ ጊዜ ለ3ዙር እንዳያሰለጥን ማገድ፡፡<br>4. በአረራተኛ ጊዜ የተቋሙን ፍቃድ መሰረዝ ፡፡ |
| 21 | ► ከባለስልጣን መ/ቤቱ ወይም ከፍቃድ ሰጪ አካል ህጋዊ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳያገኝ ስልጠና የሰጠ እና ያስተዋወቀ፡ | ✱ የጀመረው ስልጠና በአስቸኳይ እንዲያቆም ተደርጎ ለፈጸመው ድርጊት በህግ ይጠየቃል፡፡ |

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. መመሪያውን ስለማስፈፀምና የመተባበር ግዴታ

ሀ. የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች እንዲሁም የፈቃድ ሰጪ አካላት ይህንን መመሪያ ተቀናጅተው ያስፈፅማሉ።

ለ. ማንኛውም የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት።

### 18. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

### 19. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።

### 20. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 11 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ካሳሁን ኃ/ማርያም

የትራንስፖርት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር